# ትንቢተ ዮናስ (42)

## ጥናት አንድ ዮናስ 1:1-16

የጥናት ዓላማ፦ የእኛ የክርስትያኖች በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ስንጀምር፤ የራሳችንን ህይወት ከማመሳቀል አልፎ ሌሎችን ማለትም፤ ቤተሰብን፣ ጓደኛን፣ ወይም ደግሞ እንደ ዮናስ ጉዳያችንን የማያውቁትን ጭምር ሊያውክና ሊበጠብጥ እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ከዚያም ይህ ሁሉ አስጨናቂ ነገር በማን ምክንያት እንደመጣብን ንገረን፣ ሥራህ ምንድነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህስ የት ነው? ከየትኛውስ ህዝብ ነህ? አሉት›› ዮናስ 1:8

1. ዮናስ 1:1-16 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-2 ላይ ከምናየው ዮናስ ከእግዚአብሄር የተቀበለው ተልዕኮ ምን የሚል ነበረ? እግዚአብሄር በዚህ ክፍል ውስጥ ስንመለከት ወደ ዮናስ የመጣው በምን መንገድ ነው?
2. ‹‹ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ›› በማለት ቁ3 ይናገራል። ይህንን ሲል ጸሐፊው ዮናስ የእግዚአብሄር ነብይ ሆኖ እያለ በመዝ 139:7-12 ላይ ያለውን ከእግዚአብሄር ፊት የትም ሄዶ ሊሰወር እንደማይችል አያውቅም፣ ወይስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? አንተስ እግዚአብሄር የሰጠህን ተልዕኮ ላለመወጣት የምትወስደው እርምጃ ምን ይመስላል?
3. በቁ1-5 ውስጥ ለእግዚአብሄር ትእዛዝ እሺና ብለው የታዘዙትንና እንቢ ያሉትንም ለብቻ በመዘርዘር ተናገር። እግዚአብሄር በመርከቢቱና በተሳፋሪዎቹ ላይ ያመጣውን መናወጥ ለማቆም ከቁ1-8 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ተሳፋሪዎቹ የወሰዷቸው እርምጃዎች ወይም ሙከራዎች ምን ምንድናቸው?
4. ህዝቡ ሁሉ ሲራወጥ፣ ወደ አምላኩ ሲጸልይና እቃው ሁሉ ወደ ባህር ሲወረወር ዮናስ በምን ሁኔታ ላይ ይገኝ እንደነበረ ተናገር። ከእግዚአብሄር ፈቃድ ውጭ ያለ ሰው፤ እየፈለገ የነበረውን ትክክለኛ መርከብ ወዲያው ማግኘት መቻሉ፤ ይህ ሁሉ ውክቢያ እያለ ደግሞ እርሱ እልም ያለ እንቅልፍ መተኛት መቻሉን ስናይ ከዚህ ምን መማር የምንችለው እውነት አለ ትላለህ?
5. እጣው በዮናስ ላይ ሲወጣ ተሳፋሪዎቹ ስንት ጥያቄዎችን ነው የጠየቁት? የተጠየቃቸው ጥያቄዎችስ ምን ምን የሚሉ ነበሩ? ዮናስ ከተጠየቃቸው ጥያቄዎች ውስጥ መልስ በቂ መልስ ሰጥቷል ብለህ የምታምነው ለየትኞቹ ጥያቄዎች ነው?
6. ቁ10-13ትን ስናነብ ዮናስ ስለማንነቱ ለነዚህ ሰዎች ሲናገር የሰዎቹ ስሜትና ምላሻቸው ምን ነበረ? ዮናስ ለዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ መፍትሔ አድርጎ ለተሳፋሪዎቹ የነገራቸው ነገር ምንድነው? እነዚህ እግዚአብሄርን የማያውቁ አህዛብ ለዮናስ ርህራሄ ሊያሳዩ መሞከራቸውን የምናይበት ድርጊት የትኛው ነው? እግዚአብሄር ባህራችንን ካናወጠው ሰዎች ሁሉ እንኳን ቢተባበሩና ሊረዱን ቢሞክሩ መፍትሄ ሊያመጡልን እንደማይችሉ ማየት እንችላለን።
7. ቁ14-16 ላይ ሲሆን የምናያቸውን ነገሮች በራስህ ቋንቋ ተናገር።
8. ጠቅላላ ምዕራፉን ስንመለከት በሁኔታዎቹ ሲጎሳቀል የምናየው እነማንን ነው? ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነው ማን ነው? የአንተ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ በሌሎች ሰዎች ህይወት ውስጥ ሁከት ሊፈጥር እንደሚችል ይታይሃል ወይ? ሐጥያታችንና ዓመጻችን ከራሳችን አልፎ ሌሎችንም ሊያስጨንቅ የሚችል መሆኑን ልናውቅ ይገባናል።

# ጥናት ሁለት ዮናስ 1፡17-2፡10

የጥናት ዓላማ፡- ነፍሳችን በማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ ሆና ስትዝልብንና በመንፈሳችን ዝለን ጉልበት ስናጣ፤ ልንወስድ የሚገባን የመጀመሪያ እርምጃችን፤ ልክ ዮናስ እንዳደረገው ልባችንን ወደ እግዚአብሄር በመመለስ እርሱን ማሰብና መፍትሄ ወዳለው ወደ እርሱ መጸለይ እንደሚበጀን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነፍሴ በዛለች ጊዜ፤ እግዚአብሄር ሆይ አንተን አሰብሁ፤ ጸሎቴም ወደ አንተ ወደ ቅዱስ መቅደስህ አረገች።›› ዮናስ 2፡7

1. ዮናስ 1፡17-2፡10 በአንድነት ይነበብ። በምዕራፍ አንድ መጨረሻ ላይ ዮናስ ወደ ባህሩ ሲጣል እግዚአብሄር የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? እግዚአብሄር ከዮናስ ጋራ የሚዳረቀውና እንቢተኛውን በመተው ሌላ የሚታዘዝለት ሰው በመላክ ሥራውን ለመስራት ያልፈለገው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ይህ የእግዚአብሄር ባህርይ ለአንተስ በምን መንገድ ተስፋ ይሰጥሃል?
2. ማቴ 16፡4፣ ማቴ 12፡40፣ ሉቃ 11፡30 ላይ የሚገኙትን ክፍሎች በማንበብ፤ የዮናስን ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ጋራ ያነጻጸረባቸው መንገዶችና ሁኔታዎች ምን ምን እንደነበሩ አስረዳ።
3. ዮናስ በደህናው ጊዜ ሲያደርገው የማናየው ነገር ግን በዓሳው ሆድ ውስጥ ሳለ ሲያደርግ የምናገኘው ምን ሲያደርግ ነው? በቁ2 ላይ ነብዩ ወደ እግዚአብሔር የተጣራባቸውን ምክንያቶች ሲናገር የጠቀሳቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው? አንተስ አምላክህን የምትጣራው በምን ወቅት ነው? ስትጨነቅ ወይስ በሰላሙም ጊዜ ትፈልገዋለህ?
4. በ1፡15 ስናነብ ሰዎቹ ወደ ባህር እንደጣሉት ነው የምንመለከተው፤ በዚህ ክፍል ማለትም በቁ3 ላይ ስናነብ ግን ዮናስ እግዚአብሄር ራሱ ወደ ባህሩ እንደጣለው ይናገራል። እነዚህ ሁለት ክፍሎች የሚጋጩ ናቸው ወይስ ጸሐፊው ምን ሊነግረን ፈልጎ ነው?
5. ቁ2-4 በማንበብ ዮናስ በልቡ ወደ እግዚአብሄር የመመለስ ውሳኔ አድርጓል ሊያሰኘን የሚያስችለን የትኛው ሃሳብ ነው? በቁ5-6 መሰረት ዮናስ በባህር ውስጥ ስላሳለፈው ልምምድ የሚናገራቸው ነገሮች ምንድናቸው?
6. በቁ3 ላይ ‹‹ወደ ባህሩ መካከል ጣልከኝ›› በቁ6 ላይ ደግሞ ‹‹…ህይወቴን ከጉድጓድ አወጣህ›› በማለት ዮናስ ይናገራል። ይህንን አነጋገር ስንመለከት በ1ኛ ሳሙ 2፡6-7 ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ የሚስማማው እንዴት እንደሆነ ሃሳብህን ግለጽ።
7. ቁ8-10 ላይ ስናነብ ዮናስ ሲያወዳድር የምናያቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች ማንና ማን ናቸው? በጣዖት መታመን እንደ ዮናስ አነጋገር ከሆነ ትርፉ ምንድነው? በእግዚአብሄር የመታመንስ ትርፍ በዚህ ክፍል መሰረት ምንድነው ይለናል? በዚህ ክፍል ውስጥ ለእግዚአብሄር ሲታዘዝ የምናየው ነገር ምንድነው?
8. ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፤ ነብዩ ዮናስ በቁ7-8 ውስጥ እንደሚናገረው ነፍሱ በዛለችበት ጊዜ የወሰዳቸው ሁለት እርምጃዎች እንደነበሩ እናነባለን፤ እነዚህ ሁለቱ ምን ምን ነበሩ? አንተስ ነፍስህ በውስጥህ ስትዝልብህ የምትወስደው እርምጃ ምን ይመስላል? ነፍስህ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ገብታ ስትዝልብህና ግራ ስትጋባ፤ እንደ ዮናስ መለስ ብለህ እግዚአብሄርን ማሰብና፤ ከዚያም አልፈህ በጸሎት ወደ እርሱ ልብህን መመለስ መፍትሄ መሆኑን አስታውስ።

# ጥናት ሶስት ዮናስ 3፡1-10

*የጥናት ዓላማ፡- ሰው ምንም ያህል ሃጥያተኛና ከእግዚአብሄር መንገድ የራቀ ቢሆንም እንኳን፤ ከልቡ ተጸጽቶ ንስሃ የሚገባውንና ከክፉ መንገዱ የሚመለሰውን ሰው እግዚአብሄር በርህራሄ እንደሚቀበለውና ይቅር እንደሚለው ለመማር፡፡*
*የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እግዚአብሄርም ምን እንዳደረጉና ከክፉ መንገዳቸውም እንዴት እንደተመለሱ ባየ ጊዜ ራራላቸው፤ በእነርሱም ላይ ሊያመጣ ያሰበውን ጥፋት አላደረገም፡፡›› ዮናስ 3፡10*

1. ዮናስ 3፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ ዮናስ በሁለተኛው ምዕራፍ ውስጥ ከእግዚአብሄር መኮብለሉን ትቶ ወደ እግዚአብሄር ማሰብና መጸለይ እንደጀመረ ተመልክተናል፡፡ የዮናስ ልብ ወደ አምላኩ ሲመለስ በ3፡1 ላይ የእግዚአብሄር ምላሽስ ምን እንደሆነ ነው የምናየው? ከልባችን ወደ አምላካችን ስንመለስ እርሱም ወደ እኛ ይመለሳል፡፡
2. በቁ1-2 መሰረት ነብዩ ዮናስ ለነነዌ ህዝብ እንዲሰብክ በእግዚአብሄር የተነገረው ነገር ምን የሚል ነው? የመጀመሪያው ተልዕኮው ለዮናስ ስላልተስማማውና ለመኮብለል ስላበቃው እግዚአብሄር ለሁለተኛ ጊዜ ሲልከው መልዕክቱን ቀይሮታል ወይ? ለምን?
3. በ1፡3 እና በ3፡3 ላይ የምትመለከታቸውን ነገሮች ሁሉ በማነጻጸር ተናገር፡፡ ጸሐፊው የነነዌን ከተማ አስመልክቶ በዚህ ቁጥር 3 ላይ የሚናገራቸውን ሃሳቦች ዘርዝር፡፡
4. ቁ4-5 ላይ ስናነብ የዮናስ ስብከት ምን የሚል ነበረ? እግዚአብሄር ለነነዌ ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ የሰጣቸው ምን ያህል ጊዜ ነበረ?
5. የነነዌ ሰዎች ለነብዩ ለዮናስ ዐዋጅ የሰጡት ምላሽ ምን ይመስላል? የዮናስ ስብከት ርዝመቱን በሰደቂቃ ብትናገረው ምን ያህል ጊዜ የሚፈጅ ስብከት ነው? ከዚህ ሁኔታ ምን መማር የምንችለው እውነት አለ ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ6-9 ስናነብ ዮናስ ስለነነዌ ዐዋጅ በተናገረ ጊዜ ንጉሱ የወሰዳቸውን እርምጃዎች በዝርዝር ተናገር፡፡ ንጉሱና መሳፍንቱ ያወጡት ዐዋጅ የሚመለከተው ማንን ነበረ? በዐዋጁ መሰረት እንዲያደርጉ የተጠየቋቸው ነገሮች ምን ምን እንደነበሩ ዘርዝር፡፡ ከንጉሱ ትዕዛዝና ከወጣው አዋጅ ስትመለከት እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ማስጠንቀቂያ ምን ያህል አክብደው ተመልክተውታል ትላለህ? አንተስ እግዚአብሄር ሲናገርህና ሲያስጠነቅቅህ ምን ያህል አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥተህ ትታዘዘዋለህ?
7. ቁ10 ሲናገር እግዚአብሄር የነነዌ ሰዎች የተናገሩትን ንግግር ሰምቶ ነው ወይ ያሰበውን ጥፋት ከማድረግ የተመለሰው? ካልሆነስ ይህ ክፍል ምን ባየ ጊዜ ነው ይላል ያሰበውን ከማድረግ የተመለሰው?
8. በቁ10 ላይ ሲገለጥ የምንመለከተው የእግዚአብሄር ባህርይ ምንድነው? ይህ ባህርይው ጨካኝና ክፉ ለሆኑት ለአህዛብ፣ ጭምር ሲገለጥ ማየታችን ምን ሊያስተምረን ይችላል? የአንተስ ርህራሄ ለመልካምና ለተወደዱ ብቻ ነው ወይስ ለክፉዎችም ይደርሳል? አንተም በምንም ዓይነት ሁኔታ ብትገኝ፤ የእግዚአብሄርን ምህረት ፈልገህ ወደ እርሱ ስትመጣ እግዚአብሄር ለምህረት እንቢ እንደማይልህ ልትረዳ ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት አራት ዮናስ 4፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ያዘዘንን ማድረጋችንን ብቻ በመቀበል ደስ የሚሰኝ አምላክ እንዳልሆነና፤ እርሱ የሚያዘንን ማናቸውንም ነገር ስናደርግ ከበስተኋላው ያለውን መንፈሱን ጭምር እንደሚመዝን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እግዚአብሄርም ምን እንዳደረገና ከክፉ መንገዳቸውም እንዴት እንደተመለሱ ባየ ጊዜ ራራላቸው፤ በእነርሱም ላይ ሊያመጣ ያሰበውን ጥፋት አላደረገም...ዮናስ ግን ፈጽሞ አልተደሰተም፤ ስለዚህም ተቆጣ።›› ዮናስ 3፡10-4፡1

1. ዮናስ 4፡1-11 በአንድነት ይነበብ። በነነዌ ሰዎች ንስሃ መግባትና በእግዚአብሄር ይቅር ማለት፤ ዮናስ የተሰማው ስሜት ምን ይመስላል? የንስሃ ስብከትን ሰብኮላቸው ስብከቱን በመቀበል ለንስሃ መብቃት ሲችሉ ደስተኛ መሆን ሲገባው ለምን ይመስልሃል ዮናስ ከዚያ ይልቅ መከፋትን ያሳየው?
2. ዮናስ አለመደሰቱንና ቁጣውን በምን መንገድ ነው ሲገልጥ የምንመለከተው? ቁ2ትን ስናነብ ነብዩ ከአገሩ ሳይወጣ ከእግዚአብሄር ጋራ ውይይት እንዳካሄደ እናያለን። ‹‹በአገሬ ሳለሁ የተናገርኩትስ ይህን አልነበረምን?›› የሚለውን አነጋገር በትኩረት ስታጤነው፣ ከእግዚአብሄር ጋራ የተወያየው ውይይት ምን ሊሆን ይችላል ብለህ እንደምታስብ ለወገኖች አካፍል።
3. ዮናስ ወደ ተርሴስ መኮብለሉ ምክንያት አድርጎ በዚህ ክፍል የሚናገረው ነገር ምንድነው? ስለ እግዚአብሄር ባህርይ ነብዩ ዮናስ የተረዳቸው ከቁ2 ውስጥ ብቻ ቢያንስ አምስቱን በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ ባህርዮቹን በአንተ ህይወት ውስጥ የትኞቹን ተለማምደሃቸዋል?
4. በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ዮናስ ተጨንቆ ሲጸልይ እግዚአብሄር እንደማረውና ከነበረበት አዘቅት እንዳወጣው እናስታውሳለን። ታዲያ ለምንድነው ዮናስ ለራሱ ምህረት ለምኖ ሲሰጠው እንዳመሰገነ፤ እነዚህ የነነዌ ሰዎች ምህረት ማግኘታቸው የቀረቀረው? በቁ3 ላይ ስናይ የነነዌ ሰዎች ንስሃ ገብቶ ወደ እግዚአብሄር መመለስ፤ ይህንን ሰው ምን ያህል እንዳስቆጣው የምናይበት በምንድነው?
5. ለዮናስ ቁጣ የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበረ? ዮናስ ለእግዚአብሄር ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ይህች የነነዌ ከተማ ንስሃ እንደገባችና እግዚአብሄርም ራርቶ ከቁጣው መመለሱን እያወቀ፤ ለምንድነው ታዲያ ዮናስ የሚሆነውን ለማየት ራሱን አዘገጃጅቶ መቀመጡ?
6. በቁ6 ላይ እግዚአብሄር ለእርሱ ባደረገው ነገር ማለትም ከሙቀቱ ጥላ እንዲሆነው ቅል ስላበቀለለት የተሰማው ስሜት ምን ነበረ? ዮናስን በተደጋጋሚ ስናየው እግዚአብሄር ለእርሱ በጎ ነገር ሲያደርገለት ደስታውን ከመግለጥ ወደ ኋላ አይልምኝ፣ ለጠላቶቹ ግን መልካም ነገር ሲመጣ መቀበል የሚቸግረው ነብይ እንደሆነ ይታያል። አንተስ ሌሎች በሚያገኙት በረከት ደስ ትሰኛለህ ወይስ ዓይንህ ይቀላል።
7. ዮናስ ለሁለተኛ ጊዜ ከመኖር ይልቅ ሞትን ሲመርጥ በቁ8 ላይ እናያለን። እነዚህ ሞትን የተመኘባቸው ሁለት ጊዜያት በ4፡3 እና 4፡8 ላይ ያሉት የሚለዩበትን መንገድ ተናገር። በቁ6-8 ላይ እግዚአብሄር በተፈጥሮው ላይ የሚያካሂዳቸውን ነገሮች ስንመለከት ስለ እግዚአብሄር የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?
8. በቁ10-11 ከምናነበው ውይይት፤ ዮናስ እንዲገባው እግዚአብሄር የፈለገው ዋነኛ ነገር ምን እንደሆነ በአንድ ዓረፍተ ነገር በማጠቃለል ተናገር።
9. ዮናስ በሁለተኛው ጊዜ እግዚአብሄር ሲልከው እሺ ብሎ ታዞ እንደሄደና ከተማይቱ ንስሃ እንደገባች አይተናል። የተላከበትን ተልዕኮ ከተወጣ ታዲያ እግዚአብሄር ለምንድነው ዮናስን አለቅ ብሎ የሚከታተለው? ትክክለኛ ባልሆነ ልብ የታዘዝከውን አገልግሎት የፈጸምክበት ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ስለታዘዝክ ብቻ ሳይሆን በእሺታና በፍቅር መንፈስ አገልግሎቱን ጌታህን እንድታገለግል እንጂ፤ በግዴታ መንፈስ ስራውን መስራትህ ብቻ እርሱን እንደማያረካው ልትገነዘብ ይገባሃል።